የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)
Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

# ስማችን --- ኢወክንድ
# ልሳናችን---- ነቅንቅ

ግንቦት 5 ቀን 2002 ዓ.ም

## ከወያኔ መጠንቀቅ በተኩላ እንዳንነጠቅ

የጥንት አያት ቅድመ አያቶቻችንን የነጻነት የተጋድሎ መንፈስ ቀለብ አድርግን፣ የቀደምት ወንድም እህቶቻችንን የትግል ፅናት ወርሰን የተነሳን ስለሆነን ነው በኢወክንድ ስም የተደራጀነው ።

ኋላ ቀርና አምባገነን የሆኑትን ሥርዓት ሲፋለሙ ለተሰው የቀደምት ወጣቶች ከበሬታ ስላለን ነው የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ብለን የተደራጀነው።

ላለፉት 40 ዓመታት በመስዋዕትነት የታጀበ የቆራጥነት ምጥ አምጦ የወለደን የአንድ ዓመት ለጋ ድርጅት ብንሆንም፣ እሳትን ከውሃ፤ ምርትን ከግርዱ፣ አርበኛን ከባንዳ፤ ፀረ ኢትዮጵያዊውን ከኢትዮጵያን ወዳዱ የመለየትን ፀጋ በነፀጋዬ ፍዳ ፀጋን ተላብሰናልና ኩራት ኩራት ይለናል።

ታዲያ እኛ ሳንፈጠር ሕዝባዊ ገድል የፈፀሙትን ስናስታውስ ዛሬ የጊዜው አራሙቻዎች ያደረሱትን ፀረ ወጣት ፍጅት ይረሳሉ ተብለን አንደ ጌኛ መቆጠራችን ኩፉኛ ያበግነናል፤ ጭራሽ ያጠብቀናል። የኢትዮጵያ ጠላት የሆነውን ወያኔን ለማጥፋት በብዛት ያሰባስበናል።

ይህ የመርገምት ጎተራው ሞልቶ የፈሰሰ ተባይ ሥርዓት ባለፉት 19 ዓምታት የቀለቡ ማወራርጃ ያደረገው የኢትዮጵያ ወጣቶችን ደም መሆኑን ማን ይዘነጋለታል? የራሱ የገዳዩ ፍጡሮች ገፋ ሲልም ህሊናቸውን የጥቅም ሞራ የሸፈነባቸው ካልሆኑ በቀር።

- እኛ ውጣቶች በሀገራችን ተወለድንባት እንጂ መቼ ተማርንባት? ያልተመረመረ ፀረ ኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲ ፈጀን እንጂ?
- ቁቤ፤ ላቲን፣ ወጋጎዳ፣... ወዘተርፈ እያለ ወያኔ አደነቆረን እንጂ
- እኛን ወጣቶችንን ቤተ ሠቦቻችንን በዘር ምንጫቸውና በፓለቲካ አመለካከታቸው ከሥራ አፈናቅለው፤ ከቀዬአቸው መንግለው፤ በኤድስ፤ በርሃብ ፈጅተውብን አሳዳጊ አልባ አድርገውን፤ ለጎዳና ተዳዳሪነት ዳርገውን መልሰው አደገኛ ቦዘኔዎች ብለው ሠየሙን እንጂ፤
- ለዩንቨርስቲ የበቁ ወንድም፤ እህቶቻችንንም ቢሆን በ1992 ፤ በ93፤ በ95 ፤ እና በ97 ኮሌጅ መኝታ ቤታቸው ድረስ በመሄድ በትግራይ ትግርኝ ጠባብ ተስፈንጣሪ አራጆች የወንድም እህቶቻችን ደም ፈሠሠ እንጂ፤ ይህን መቼውንስ ዘንግተን ነው፤
- በሕዝብ ደም የጠገቡ የዘመኑ ዘረኛ ሰካራሞች ባነሱት የዘር ጠብና አምባጓሮ የጥጋባቸው ማብረጃ፤ የዛራቸው መማለጃ ይሆን ዘንድ ባድሜ ላይ 100.000 ወጣቶችን በከንቱ አስፈጁት እንጂ፤
- አዋሣ ሎቄ መግቢያው ላይ የኮባ ቅጠል ይዘን ሰላማዊ ሠልፍ ስናደርግ 300 የምንሆን ወጣት ልጆች በወያኔ ተፈጀን እንጂ ፤
- ወጣት እህቶቻችንን የግፍ ሰለባ አድርገው፣ በገዛ ሀገራቸው መቆሚያ መሄጃ አሳጥተው የአረብ ሀገር ገረድ ለመሆን በወያኔ ኩባኒያ ከነነፍሳቸው ለከባድ ሥራና ለቱጃሮች ወሲብ ማርኪያ ተሸጡ እንጂ፤ መቼ የወያኔ ሥርዓት አሰበላቸው?

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com

- ከገቡ ጀምሮ ለ19 ዓመት ይፈጁናል፣ ያስፈጁናል፣ ያስርቡናል፣ ለዕፅ ይዳርጉናል፣ ሴቶችን ለሽርሙጥና ያመቻቹናል፣ በዘር ያጫርሱናል፣ እንጂ መቼስ የኛ ሆነው ነው? ዛሬ ላይ ቆመው መልሰው የኢትዮጵያ ወጣቶች ሊግ እያሉ ልጋጋቸውን የሚተፉብን ፤

በኛ እምነት ወያኔ ኢትዮጵያዊ ሆኖ የኢትዮጵያን ወጣቶች ሊያደራጅን ቀርቶ ሊያስበን መከጀሉ ይበልጥ ያስጠይፈናል እንጂ ልባችንን ከቶውንም አያገኛትም።

- የሃያ አንድ ዓመቱ ወጣት አለምአንት አመንጋ በፐ/ር አሥራት ቀብር ላይ ዘመርክ ተብሎ የተገደለው በወያኔ፤
- ወጣት ስንታየሁ ታደሰ አባ ገ/ መድህንን ተቃወምክ ተብሎ ልደታ ቤተክርስቲያን የተገደለው በወያኔ፤
- ኤርትራ መለየት የለባትም ስላለ ወጣት ተስፋሁን በሣንጃ የታረደው በወያኔ
- ወጣቱ ባህታዊ ፈቀደ ሥላሴ ተስፋዬ  የተገደለው በወያኔ ፤
- አሰፋ ማሩንና ተስፋዬ ታደሰን ቀስፎ ልጆቻቸውን ወላጅ አልባ ያደረገው ወያኔ ፤
- ጎንደር አደባባይ ኢየሱስ ወጣት መዘምራንን ጨፍጭፎ የረፈረፈው ወያኔ፤
- በአንዋር መስጊድ ወጣቶችን የፈጀው ወያኔ
- በ97 ምርጫ የ21 ና የ17 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የነበሩ ሴት ወጣቶቻችን ሽብሬ ደሳለኝና መሠረት ታደሰን፣... የቀጨው ወያኔ ፤
- በምርጫ ተሸንፎ ሲያፍር ተቃውሟቸውን ያሰሙትን በመቶ የሚቆጠሩ ወጣቶችን የፈጀ ወያኔ፤ 30000 ወጣቶችን ዴዴሳና ዙዋይ ላይ ለአዞና ለጊንጥ ያሰጣ ወያኔ፤
- አሁን እንኳን በቅርቡ ቱጃሩ አላሙዲና ወያኔ እያደርጉ ያሉትን ዘረፋ በመቃወማቸው     የሻኪሶ ወጣቶችን ተኩስ ከፍቶ የገደለው ወያኔ

እንዴት ያለ የሞራል ብቃት ኖሮት ነው በሰላይ ልጆቹ አማካኝነት በዓለም ዙርያ የወጣቶች ሊግ አዋቅራለሁ የሚለን?

‘ጎበዝ ተንቀናል ዘጠኝ ሞት መጣ’ ቢሉት አንዴ ግባ በለው እንዳለው ጀግና አንድ ነፍስ ይዘን ዘጠኝ ጊዜ ሞት፤ መፍቀድ የለብንም። ውርደትም ሞት ነው፤ ባርነትም የከፋ ሞት ነው፤ ተገዥነትም ሌላው አይነት ሞት። ስለዚህ እኒህ ወያኔዎችና ዲቃላዎቻቸው እኛ ወጣቶችን ሊደፍሩ ሲከጅሉ አይገባም ነው መፈክራችን። መደራጀትና ተደራጅቶም መታገል ኢትዮጵያን ከዘመናዊ ባርነት ያድናታልና፤ ኢወክንድ ኢትዮጵያዊ ነፍስ ያለው የወጣት ድርጅት ስለሆነ ፈልጉንና እንደባለቅ፤ ለሀገር ስንል።

‘ኢትዮአሜሪካን አክሽን ሊግ’፤ ‘የወጣቶች ሊግ’ ምንትስ እያለ ወያኔ ከሀገር እስከውጪ በኢትዮጵያዊ ሽማ ተደርቦ ሲመጣ ሽማውን ገፈን ዕርቃኑን እናስቀራለን እንጂ በሚሰምጠው የወያኔ መርከብ ተሳፋሪ እንዳማንሆን በቁርጠኝነት መግለጽና ማሳፈር አለበን ሲል ለኢትዮጵያ ወጣቶች ኢወክንድ መልዕክት ያስተላልፋል።

ያለቀለት የወያኔ ሥርዓትን በወጣት ወያኔ ሊግ ለመጠገን  የሚደረገውን ጉድ ጉድ በኢወክንድና በሌሎች ሀገር ወዳደ ኢትዮጵያዊ ወጣቶች ክንድ ይገደባል።

የኢትዮጵያን ወጣቶች ጠላት የሆነውን ወያኔን
በክንዳችን እናስወግዳለን።

Tel 202-291-5832    P.O.Box 56068    Washington DC 20040        e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com